# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 163 ሰኔ 23 2003 ገጽ 1


**መለስ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ኦጋዴንንም የሚፈልገው ለጥቅሙ ሲል ብቻ ነው። በይስሙላ ፌደራሊዝም ኦጋዴን "የሶማሊ ክልላዊ መንግሥት" ቢባልም የሚተዳደረው ግን እንደሌላው ቦታ ሁሉ ከአብራኩ በወጡ ምስለኔዎቹ አማካይነት በትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላት ነው።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ዕውቀትና ችሎት ያላቸው የህግ ሙያተኞች በወያኔ ፍርድ ቤቶች ተቀጥረው ላለመስራት መወሰናቸው ታወቀ

በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የፍትህ አሠራር የተማረሩ ዕውቀትና ችሎታ ያላቸው የህግ ሙያተኞች በወያኔ ፍርድቤቶች ተቀጥረው ለመሥራት አለመፈለጋቸውን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝደንት ተገነ ጌታነህ ባለፈው ሳምንት ለተወካዮች ምክር ቤት ተብዬው ካቀረበው ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል።

እንደ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ፕሬዝደንት ጌታነህ ሪፖርት ፤ በተለያዩ ወቅቶች በአገዛዙ የተሾሙና ልምድ ያካበቱ ዳኞች ሥራ በመልቀቃቸው ምክንያት፡ በሁሉም የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ከፍተኛ የሆነ የዳኞች እጥረት አጋጥሞአል። ከዚህም በተጨማር በሥራ ላይ የቀሩትን ባለሙያዎች ይዞ ማቆየት ካለመቻሉም በላይ፣ በሚለቁት ባለሙያዎች ምትክ ሙያተኛ ሰው ፈልጎ ማግኘት አለመቻሉ ሌላው ችግር እንደሆነ አቶ ተገኔ አልሸሸገም።

የባለሙያ ችግር በሁሉም የፍርድ ቤት የሥራ መደቦች ያለ መሆኑን የገለፁው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት፣ሠራተኛ ለመቅጠር በተደጋጋሚ ጊዜ የቅጥር ማስታወቂያ ቢወጣም የሚቀጠር ይቅርና ለውድድር የሚቀርብ አመልካች እንኳን ማጣት የተለመደ እየሆነ መምጣቱን አመልክቶአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የወያኔ አገዛዝ 8 ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በህገ ወጥ መንገድ ከአገር አሸሽቶአል በማለት የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም የወጣው ሪፖርት በወያኔ መሪዎች መንደር ድንጋጤን መፍጠሩ ተዘገበ

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ተራዲኦ ፕሮግራም ፋሽስቱ መለስ ዜናዊና ሃይለማሪያም ደሳለኝ በተካፈሉበት የ ኢስታንቡል ስብሰባ ለህዝብ ይፋ ያደረጉት የ8 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር በህገ ወጥ መንገድ ከአገር መውጣት ጉዳይ በወያኔ መሪዎች ውስጥ ትልቅ ድንጋጤ መፍጠሩን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴለቪዥን በትናንትናው የዜና እወጃ ዘግቦአል።

ኢሳት የታመኑ ምንጮቹን ገልጾ በዘገበው በዚህ ዜና፤ የመንግስታቱ ድርጅት የልማት ፕሮግራም ይፋ ስላደረገው ቅሌት የሚዘግቡ የአገር ውስጥ ጋዜጦችና ዜና ዘጋቢዎች መረጃውን በህበረተሰቡ ውስጥ በስፋት እንዳያሰራጩ ለመከላከል ጥብቅ ቁጥጥር እንዲደረግባቸው ፤ ይህንን ተላለፈው መረጃውን አሰራጭተው በተገኙት ላይ ደግሞ ሰበብ ተፈልጎ ወዲያውኑ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለፖሊስ ባለስልጣናት መመሪያ ተላልፎአል።

እንደ ኢሳት ምንጮች መረጃ የወያኔ ባለሥልጣናት ይህንን አይነት የተስፋ መቁረጥ እርምጃ እንዲወስዱ ያነሳሳቸው፤ አንዳንድ በአገሪቱ የሚታተሙ ፕሬሶች የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም ይፋ ያደረገውን ሪፖርት መዘገባቸውን ተከትሎ፤ ወሬው በስፋት በመዛመቱና በወያኔ ፕሮፖጋንዳ ተወናብዶ ለዓባይ ግድብ ተብዬው ፕሮጀክት የሞራልና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ጀምሮ የነበረው የህበረተሰብ ክፍል በንዴት ድጋፉን በማቆሙ ነው ተብሎአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ኦብነግ በኦጋዴን ክልል ተጠልፈው የነበሩትን ሁለት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዕርዳታ ሠራተኞችን እንዳስረከበ አስታወቀ

የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር ኦብነግ ባለፈው ሰኞ ሰኔ 20 ቀን ባወጣው መግለጫ ከወር በላይ በክልሉ ታግተው የሰነበቱትን ሁለት የአለም አቀፍ ድርጅቱን ሠራተኞች ማስረከቡንና የወያኔ ወታደሮች ርክክቡን ለማደናቀፍ አድርገውት የነበረውን ተከታታይ ጥቃት ማክሸፉን አስታወቀ።

የወያኔ አገዛዝ የኦብነግን የድጋፍ መሠረት ለማድረቅ በተከተለው እርምጃ ምንም አይነት የምግብና ህክምና ዕርዳታ አገልግሎት የሚሠጡ የአገር ውስጥና የውጪ ድርጅቶች በክልሉ ውስጥ እንዳይንቀሳቀሱ በማገዱ በርካታ ሽማግሌዎች፤ ህጻናትና ሴቶች በከፍተኛ ረሃብ እንደቅጠል እየረገፉ መሆናቸውን ታዋቂው የሰብአዊ መብቶች ተከራካሪ ድርጅት ሂውማን ራይትስዎች በተደጋጋሚ ከመዘገቡም በላይ በኦጋዴን ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለው የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደሆነ ገልጾ በአስቸኳይ እንዲቆም በተደጋጋሚ ጠይቆአል።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የምግብ ፕሮግራም በክልሉ በረሀብ ለተጎዱ ወገኖች ስንዴ በማከፋፈል ተግባር ላይ ተሰማርቶ የነበረ ሲሆን፣ በወያኔ እገዳ ምክንያት አገልግሎቱን እንዳቋረጠ ለማወቅ ተችሎአል።

ሰሞኑን በሲ ኤን ኤን አይ ሪፖርት ላይ ለህዝብ ይፋ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## የተቃዋሚዎችን አስተያየት ቪ ኦ ኤ እንዳያስተላለፍ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ መጠየቁ አገዛዙ የደረሰበትን ከፍተኛ ፍርሃትና ጭንቀት ያመለክታል ተባለ

በሰሜን አፍሪካ በተቀሰቀሰው የጸረ አምባገነንነት ህዝባዊ አብዮት ከፍተኛ ስጋት የገባው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ፤ ነጻነት የጠማው የኢትዮጵያ ህዝብም ተመሳሳይ እርምጃ ይወስዳል በሚል ፍርሃት በአገር ዉስጥ ከሚያካሄደዉ ይህ ነዉ የማይባል የመረጃ አፈና በተጨማሪ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ በዉጭ አገርና በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን አስተያየት ለህዝብ እንዳያሰማ የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ ጣቢያን ደጋግሞ መማጸኑ አገዛዙ የደረሰበትን ከፍተኛ የተስፋ መቁረጥና የመረበሽ ደረጃ ያመለክታል ሲሉ የተለያዩ አስተያየት ሰጪዎች ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ።

እንደ ብዙ አስተያየት ሰጪዎች አስተያየት ፤ የመድበለ ፓርቲ ስርአትንና የዜጎችን ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ መብት ህገመንግሥቱ ላይ ያሰፈረው የወያኔ አገዛዝ፤ የመድበለ ፓርቲ ሥር አት እከተላለሁ የሚለው የሚለዉ ከንቱ አባባሉ ከምርጫ 97 ወዲህ እርቃኑን እንደቀረ ብዙዎች ይስማሙበታል፤ ይህ ዘረኛ አገዛዝ ሌሎች እንዲያከብሩለት የሚፈልገውን የራሱን ህገ መንግሥት በግልጽ የሚቃረኑ ህጎችና ደንቦችን ሲያወጣ እንደቆየም በግልጽ የሚታወቅ የአደባባበይ ሚስጥር ነዉ፤ ሆኖም ይህ ጉደኛ ስርዐት አገር ውስጥ ያሉትን ሚዲያዎች ከማፈን አልፎ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮን የመሰለ ሚዛናዊ ሚዲያ የተቃዋሚዎችን ሃሳብ ለህዝብ አታሰሙምብን ብሎ እንዲህ በግልጽ ይማጸናል ብሎ የገመተ ማንም አልነበረም ብለዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም አይ ኤም ኤፍ በኢትዮጵያ ለተከሰተው እጅግ ከፍተኛ የዋጋ ግሽበት ተጠያቂው ራሱ የኢትዮጵያው አገዛዝ ነው አለ

በኢትዮጵያ ለተከሰተው ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ግሽበትና የኢኮኖሚ ቀውስ ተጠያቂው የኢትዮጵያ አገዛዝ ነው በማለት ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም አይ ኤም ኤፍ መግለጹን አሶሺየትድ ፕሬስ የሚባለዉ የዜና ወኪል ዘገበ። የዜና ወኪሉ በሃገሪቱ ለተከሰተው ቀውስ መንሴው የኢትዮጵያው አገዛዝ እንደሚለው የዓለም የምግብ ገበያ ዋጋ መጨመር ሳይሆን ከአገሪቱ አቅም በላይ ወደ ሃገር ውስጥ ያለገደብ እንዲፈስ እየተደረገ ያለው የብድር ገንዘብና በሃገሪቱ እየታተመ ያለው የገንዘብ ብዛት ነው ሲል ተቋሙ መግለጹ ተዘግቧል።

አሶሺየትድ ፕሬስ በመሬይ ስቴት ዩኒቨርሲቲ መምህር የሆኑት ኢትዮጵያዊው ፕሮፌሰር ሰይድ ሃሰን በአንድ ሃገር ውስጥ የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር በማሰብ በሸቀጦች ዋጋ ላይ አስገዳጅ የሆነ የዋጋ ተመን ማውጣት የቂሎች ተግባር ነው፣ የኢትዮጵያ መንግስት የሸቀጦችን የዋጋ ተመን በድንገትና በአስገዳጅነት ያወጣው ምንም አይነት በቂና ተገቢ የሆነ ጥናትን ሳያደርግ ኢትዮጵያዊያን በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ተቃውሞና ብስጪት እንዳይገልጹ ለማፈን በሚል ብቻ እንደሆነ ሳይታለም የተፈታ ነው ማለታቸውን አክሎ ገልጿል።

በኢትዮጵያ የሚገኙ ሸማቾችና ሻጮቸ በአሁኑ ሰአት በኢትዮጵያ እየታየ ያለውን የዋጋ ግሽበት አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ አገዛዙ የዋጋ ማስተካከያ ተመን በሚል የወሰደው ርምጃ እንደሆነ በስፋት እንደሚናገሩ አሶሺየትድ ፕሬስ አክሎ ገልጿል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በመሰረታዊ የምግብ ፍጆታዎች ላይ የወሰደው የዋጋ ማስተካከያ እርምጃ የምግብ ሸቀጦቹን ዋጋ ከሚገባው በላይ በማናሩ በጣት ከሚቆጠሩና እጅግ በጣም አናሳ ከሆኑ የአገዛዙ አባላትና ደጋፊዎች ውጭ ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የኑሮ ውድነቱ ከሚችለው በላይ ሆኖበታል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኤፈርት ኩባንያ አካል የሆነው ሳባ ኢንጂነሪንግ የአስራ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር እዳ ያለበት መሆኑ ታወቀ

ከህወሃት የንግድ ድርጅቶች አንዱ የሆነው ሳባ ኢንጂነሪንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወያኔ በመንግሥት ይዞታ ሥር የነበሩትን ንብረቶች ወደ ግል ለማዛወር ባወጣው ደንብ ከአራት አመታት በፊት ከመንግሥት በርካሽ ዋጋ የገዛውን የአዲስ ጡብ ማምረቻ ፋብሪካ ክፊያ ዋጋ እስከዛሬ ባለመፈጸሙ ክስ የቀረበበት መሆኑን ለአገዛዙ ቅርበት ያለዉ የሪፖርተር ጋዜጣ ዘገበ። እንደ ሪፖርተር ዘገባ ሳባ ኢንጂነሪንግ በገባው ውል መሰረት ክፍያውን በወቅቱ ባለመክፈሉ የ11.4 ሚሊዮን ብር ባለ ዕዳ መሆኑ ታውቋል።

በመንግሥት ቁጥጥር ሥር የነበሩትን አብዛኛዎቹን የንግድና የማምረቻ ተቋሞች በሽያጭ ስም ወደራሱ የግል ድርጅት ያዞታ ያዛወረው የትግራይ ጉጂሌ በ1999 ዓም አዲስ ጡብ ማምረቻ ፋብሪካ የተባለውን የልማት ድርጅት ለመሸጥ የይስሙላ ጨረታ ያወጣ ሲሆን፣ ሳባ ኢንጂነሪንግ ጨረታውን አሸንፎ ድርጅቱን በ23 ሚሊዮን ብር ለመግዛት በመስማማት ጥቅምት 29 ቀን 1999 ዓ.ም. የግዢ ውል ተፈራርሟል ተብሎ ነበር፡፡ በወቅቱ ሳባ ኢንጂነሪንግ የሽያጩን ዋጋ 35 በመቶ የሆነውን 8,052,000 ብር ብቻ ከፍሎ ፋብሪካውን እንዲረከብ ከተደረገ በኋላ ቀሪውን 14.9 ሚሊዮን ብር በ5 አመት (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ሰቆቃ በኦጋዴን፤ በቃ!!!

በምሥራቁ የአገራችን ክፍል - ኦጋዴን - ሰቆቃ በዝቷል!!! በደል በዝቷል!!! እሮሮ በዝቷል!!! መከራ በዝቷል!!! ግፍ በዝቷል!!! እነዚህ ሁሉ ግፍ ደግሞ አመጽን ይወልዳሉ፣ ወልደዋልም። አሁንም ኦጋዴን ምጥ ውስጥ ናት፤ ነገ የምትወልደውን መገመት አዳጋች ነው።

ቀብሪደሃር፣ ገላልሼ፣ ዋርዴር፣ ገላዲ፣ ቀላፎ፣ ጎዴ፣ አዋሬ፣ ጋሻሞና ኩርሚስ እንደድሮው የሰዎች መኖሪያ መንደሮች መሆናቸው ቀርቷል። መንደሮች ፈርሰው የወታደር ካምፓች ተገንብተው የአካባቢው ነዋሪዎች እየታደኑ ስቃይ የሚቀበሉባቸው ገሃነሞች ሆነዋል። በአካባቢው ነዋሪ ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ የሰው ልጆች ሊሸከሙት ከሚችሉት በላይ ሆኗል።

የኦጋዴን ወገኖቻችን በሁለት ጠላቶች ዒላማ ውስጥ ናቸው። በአንድ በኩል የመለስ ዜናዊ ታማኝ ጦር በቦታው ተሰማርቶ ወጣቱን ከአረጋዊ፤ ህፃኑን ከሽማግሌ፤ ወንዱን ከሴት ሳይለይ እየጨፈጨፈ ነው። የመለስ ጦር የኦጋዴንን ህዝብ ብቻ ሳይሆን ግመሎቹን፣ ከብቶቹንና መንደሮችን እያነደደ ነው። ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ሠራዊት ውስጥ እጅግም በማይታወቅ ነውረኛነት የኦጋዴንን ልጃገረዶች ዘግናኛ በሆነ መንገድ በመለስ ወታደሮች እየተደፈሩ ነው። ይህ ግፍ የት ያደርሰናል?

በሌላ በኩል ደግሞ ተፈጥሮ ለእነዚሁ ሰዎች፣ ከብቶችና መንደሮች ርህራሄን አላሳየችም። ኦጋዴን ከቀድሞው የባሰ ፍጹም በረሃ ሁናለች። በሌላ የኢትዮጵያ ግዛቶች እንደሚያደርጉት ግብረ-ሰናይ ድርጅቶች ኦጋዴንም ውስጥ የእርዳታ እጆቻቸውን መዘርጋት አልቻሉም። የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የእርዳታ ድርጅቶች በክልሉ እንዳይንቀሳቀሱ አግዷል። በልዩ ሁኔታ የተፈቀደላቸው ጥቂት የእርዳታ ድርጅቶች ቢኖሩም የሚደረግባቸው ቁጥጥር የሚያላውሳቸው አይደለም።

ኦጋዴን ወጣቶቿን አጥታለች። አሁን በአካባቢው የሚገኙ የኦጋዴን ተወላጆች ሞታቸውን እየጠበቁ ያሉ፤ የተራቡና በእድሜ የገፉ አረጋዊያን እና ህፃናት ብቻ ናቸው። የኦጋዴን ወጣቶች ከፊሎቹ በመለስ ዜናዊ ታማኝ ወታደሮች ተገደለዋል፤ ከፊሎቹ ታስረዋል። የበረቱት ነፍጥ አንስተው የመለስን አምባገነን መንግሥት እየተዋጉ ነው። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች የአያት የቅድመ-አያቶቻቸውን መንደር ጥለው ርቀው ተሰደዋል።

አሁን ኦጋዴንን የሞሏት ሊዘርፏትና ሊያዋርዷት የመጡ የመለስ ዜናዊ ሠራዊቶች አባላት ናቸው። የመለስ ዜናዊ ወታደሮችና ሰላዮች ጎረቤት አገራት ድረስ እየዘለቁ የኦጋዴንን ታጋዮች ይገድላሉ። ሰኔ 13 ቀን 2003 ዓ. ም. የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አውጭ ግንባር (ኦብነግ) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ አብዱላሂ ሰዒድ በናይሮቢ ከተማ በመለስ ዜናዊ ሰላዮች መገደላቸው የሁኔታው አስከፊነት የቅርብ ጊዜ ማሳያ ነው። ይህ ሁሉ የኦጋዴን ህዝብን ምሬት አብዝቷል። ምሬት ሲበዛ ደግሞ ይገነፍላል።

መለስ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ኦጋዴንንም የሚፈልገው ለጥቅሙ ሲል ብቻ ነው። በይስሙላ ፌደራሊዝም ኦጋዴን "የሶማሊ ክልላዊ መንግሥት" ቢባልም የሚተዳደረው ግን እንደሌላው ቦታ ሁሉ ከአብራኩ በወጡ ምስለኔዎቹ አማካይነት በትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላት ነው።

ስለውሸት ፌደራሊዝም ለሃያ ዓመታት ስንሰማ በመከረማችን ሁላችንንም ሰልችቶናል። ሃቁ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ወርሮ የያዘውን አገር ከራሱ ብቻ በወጡ ሰዎች በሚመራ ሠራዊትና የስለላ ተቋም አማካይነት እየገዛ፤ ሃብቱን እየመዘበረ መሆኑ ነው። ይህንን የብዝበዛ ሥርዓትን ነው በየአካባቢው ለመለመላቸው ተላላኪዎቹ የይስሙላ ሹመት እየሰጠና የተጋጠ አጥንት እየጣለ "ፌደራሊዝም" እያለ የሚጠራው። ኦጋዴንም ላይ በፌደራሊዝም ስም እየደረሰ ያለው በደል ይህ ነው። ይህ በደል በሁሉም የአገራችን ክልሎች እየደረሰ ያለ በመሆኑ ህመማችን የጋራ ነው።

በኦጋዴን ከርሰ ምድር ውስጥ የነዳጅና ጋዝ ክምችት አለ የሚል ግምት መኖሩ የዛሬዎቹን አርብቶ-አደር ወገኖቻችንን ህይወት አደጋ ላይ ጥሎታል። መለስ ዜናዊ መላው የአካባባቢው የከርሰ ምድር ሃብት ሲያጫርት ቆይቶ ሰሞኑም ለቻይና መንግሥት ለመስጠት ስምምነት ላይ መድረሱ ይወራል።

ግንቦት 7፡ የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ በሶማሌ ክልል - ኦጋዴን - ውስጥ የመለስ አገዛዝ እያደረሰ ያለው የዘር ማጥፋት ወንጀልን አጥብቆ ይዋጋል።

የኦጋዴን ህዝብ ወገናችን ነው። በክፉም በደጉም ጊዜ አብረን እንቆማለን፤ አብረን እንዘልቃለን። መለስና ተባባሪዎቹ አስወግደን በምንፈጥራት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ውስጥ የኦጋዴን ህዝብ ሁነኛ ቦታ እንደሚኖረው እምነታችን ነው።

በኦጋዴን ህዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን የዘር ማጥፋት በአስቸኳይ ለማስቆም ዛሬውኑ እንነሳ!!! የመለስ አገዛዝ በቃን !!!

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

---

### ዕውቀትና ችሎት ያላቸው የህግ ሙያተኞች በወያኔ ፍርድ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በመለስ ዜናዊ ቀጪን ትዕዛዝ በሚዘወረው የዳኝነት ሥርዓት ውስጥ ለማገልገል ፍላጎት ያላቸው ሙያተኞች ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ ሂዶ መደበቅ ከማይችልበት መድረሱን ፍንጭ የሰጠው ይህ ሪፖርት ፤ የችግሩን መንጭ ለዳኞች የሚከፈለው ደመወዝ ስኬል አለመስተካከልና የተመቻቸ የስራ አካባቢ ያለመኖር ነው በማለት ለማድበስበስ ሞክሮአል። ሆኖም "የተመቻቸ የሥራ ቦታ አለመኖር" የሚለው አገላለጽ ለመለስ ዜናዊ ታማኝ ሆነው ከላይ በሚመደቡ የፍትህ አካላት ሹሞች አማካይነት የፖለቲካ ተቀናቃኞችን ለማጥፋት በተግባር ላይ እየዋለ ያለው ቀጥተኛ ጣልቃ ገብነት በባለሙያዎቹ እንዳልተወደደና በዚህም ምክንያት ሥራቸውን ጥለው እንደሸሹ የሚያመለክት መሆኑን በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለረጅም ጊዜ ያገለገሉና ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የህግ ባለሙያ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

እኚሁ ባለሙያ አክለውም ዳኝነት የህሊና ነፃነትን ይጠይቃል፤ የህሊና ነፃነት የሌለዉ ዳኛ ፍትህ ሊሰጥ አይችልም። በሰዉ ህይወትና ንብረት ላይ ልዩነት ሊያስከትል የሚችል ዉሳኔ የሞራል ጥንካሬን ይጠይቃል፤ በኢትዮጵያ ያለዉ የፍትህ አካሄድ የሞራል ድቀት ያለባቸዉ ብቻ ሊሸከሙት የሚችሉት ነዉ። የህሊና ነፃነት ሳይኖረዉ የሞራል ድቀት እየደረሰበት ዳኝነት እሰጣለሁ ብሎ ችሎት የሚቀመጥ ህግ አዋቂ በፍፁም ሊኖር አይችልም ፤ ይህ አገዛዝ ሥልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ አንስቶ እያደረገ ያለው ግልጽ የሆነ ጣልቃ ገብነት ፍትህን ከማዛባት አልፎ የዳኝነት ሥራ ላይ የተሰማሩትን ሂሊና ያዋረደ ነው ብለዋል።

አንጋፋው የህክምና ባለሙያ የነበሩትንና የመላው አማራ ህዝብ ድርጅት መሥራች ፕሮፌሰር አሥራት ወልዴየስ ላይ የፈጠራ ወንጀል ተመስርቶ በፍርድ ቤት ውሳኔ ወህኒ ወርደው ለህልፈት ከበቁ ጊዜ ጀምሮ በቅርቡ በሽብርተኝነት ወንጀል ተከሰው እስከ ዕድሜ ልክ የሚደርስ እሥራት የተፈርዶባቸው የኦነግ ተጠርጣሪዎች ባለው የፖለቲካ ክስ ዳኝነት የሰጡት የህግ ሙያተኞች የአገሪቱን ፍትህ ሥር ዓት ብቻ ሳይሆን ያዋረዱት የራሳቸውንም ስብ ዕናና ሙያ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ።

### ኦብነግ በኦጋዴን ክልል ተጠልፈው የነበሩትን ሁለት የተባበሩት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የሆነው የቪዲዮ ምስል በ1977 በአገራችን ደርሶ ከነበረው አስከፊው የድርቅ ረሃብ በከፋ ሁኔታ ዜጎችና የቤት እንስሳት በምግብና ውሃ እጦት በሚያሳዝን አሟሟት እየረገፉ መሆኑን አሳይቶአል። መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ የአገሪቱን ሃብትና ንብረት ዘርፈው በልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ሥም በየፈረንጅ አገር ሲያጠራቅሙ ህዝብ ለ እንዲህ አይነት የከፋ ሰቆቃ መዳረጉ ይዋል የደር እንጂ እንደሚያስጠይቅ ይታወቃል።

### የወያኔ አገዛዝ 8 ነጥብ 4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በዓባይ ግድብ ዙሪያ የህዝቡ ስሜት እጅግ መቀዝቀዙ ያስደነገጣቸው አንዳንድ የኢህአዴግ አባላት የሆኑ የቀበሌና የወረዳ አመራሮች፤-"በህዳሴው ግድብ ግንባታ እንድትሳተፉ የተፈለገው፤ የኔነት ስሜት እንዲሰማችሁ ነው እንጂ፤ ኢህአዴግ ገንዘብ ስለቸገረው አይደለም፤የእናንተ ገንዘብ መጣ፤ቀረ ፤የሚያመጣው ለውጥ የለም!ኢህአዴግ በቂ ገንዘብ አለው" በማለት ነዋሪዎችን በሀይለ-ቃል መናገር እንደጀመሩም- የኢሳት ምንጮች መጠቆማቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ይፋ ባደረገው ሪፖርት መሰረት፤ በዘመነ-ወያኔ ለኢትዮጵያ በእርዳታ ከተለገሰ ገንዘብ መካከል እስከ 2008 በነበረው ጊዜ 8 ነጥብ 4 ቢሊዮን ዶላር ወይም 150 ቢሊዮን ብር ተዘርፎ፤ በባለስልጣናት ቤተሰቦችና በነጋዴ ጓደኞቻቸው ስም፤በውጪ አገር ባንኮች ተቀምጧል።

የኢሳት ዘጋቢ ያነጋገሯቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች፡-"ነገሩ አሳዛኝና አሳፋሪ ቅሌት ነው።ሙስና ሊኖር እንደሚችል ብንገምትም፤ በዚህ መጠን እንዘረፋለን ብለን በጭራሽ ገምተን አናውቅም።ዘርፈውናል ከማለት ገድለውናል ብንል ይሻላል። ዳቦ አጥተን በረሀብ መቃጠል የጀመርነው፤በእግዜር ቁጣ ሳይሆን፤ በነሱ ጭካኔ እንደሆነ በደንብ እየገባን ነው" ማለታቸውን ኢሳት ዘግቦአል።

የአውራምባ ታይምስ አዘጋጅ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ፤ ለእስር ከመዳረጉ ሁለት ቀናት በፊት ለንባብ በበቃው ጋዜጣ ላይ፤ "ሽሚያው የት ለመድረስ ነው?" በሚል ርዕስ፤ መረን ስለለቀቀው የህወሀት መሪዎች ሙስና በስፋት ማስነበቡን ይታወሳል።

### የተቃዋሚዎችን አስተያየት ቪ ኦ ኤ እንዳያስተላለፍ የመለስ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የመለስ ዜናዊን አፈጮሌነት ከማያቋርጠዉ ንግግሩ ብቻ በመስማት ሰውዬውን አዋቂ አድርገው ያደንቁት የነበሩ ደጋፊዎቹና ምዕራባዉያን አጋሮቹ ሳይቀር ይህንን የመሰለ አሳፋሪ የዲፕሎማሲ ቋንቋ ሲሰሙ ምን ሊሰማቸው እንደሚችል መገመት ይከብዳል ያሉት አንድ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ መምህር ፤ ጠቅላይ ሚኒስትራችን የዕውቀት አድማሳቸውን ተጠቅመው ጨርሰው የኋሊት ጉዞ ጀምረዋል፤ ይህ ደግሞ አማካሪዎቻቸዉንና በዙሪያቸው የተሰለፉትን ሁሉ የሚ ሳፍር ጉዳይ ነዉ በማለት የተሰማቸውን ሃዘን ገልጸዋል።

ሌላው አስተያየት ሰጪ ደግሞ መለስ ዜናዊና አማካሪዎቹ ከ17 አመት የጫካ ትግል ቦኋላ በድል ከተማ ይግቡ እንጂ በስነልቦናም ሆነ በመንፈስ አስተሳሰባቸው አሁንም ገና ጫካ ውስጥ ያሉ ከሚያስመስላቸው ድርጊቶች አንዱ ይህ ለቪኦ ኤ ያቀረቡት "የተቃዋሚዎችን አስተያየት ለህዝብ አታሰሙብኝ" የሚለዉ አቤቱታ ነው ካሉ ቦኋላ የሰው ልጅ መረጃ የማግኘት ነጻነቱ በቦታና በጊዜ ልዩነት ሊገደብ ከማይችልበት የኢንፎርሜሽን ቴኪኒ ኦሎጂ ዘመን ላይ መሆናችንን የሰሙም አይመስልም ብለዋል።

---


**የፖስታ ሳጥን ቁጥር :-** POBox: 4916 2003EX Haarlem, The Netherlands

## ለወጣቶች

### ነጻነታችንን የእፍኝት ልጆች ሊከለክሉን አይገባም!!! (ከዝግጅት ክፍላችን)

የትላንት ወጣቶች የተውልን ኢትዮጵያ ዛሬ በእፉኝት ልጆች እጅ በመውደቋ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያሉ ዜጎቿ ነጻነታቸውን ተገፈው ከሰው በታች ሁነው ለመኖር ተገደዋል።ይህችን ኢትዮጵያ ነገ የሚረከቧት የዛሬዎቹ ወጣቶች ናቸው።

ዛሬ በአገራችን ውስጥ በተንሰራፋው ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖሊቲካዊ ቀውሶች ግንባር ቀደም ተጎጂው ወጣቱ ነው። የተሻለ ህይወት ፍለጋ አገሩን ጥሎ የጦርነት አውድማ በሆነችው ሱማሊያ በኩል ሳይቀር ድንበር እያቋረጠ በመሸሽ ላይ ያለው አብዛኛው ዜጋ ወጣት ነው። ወያኔ በስውር ባቋቋማቸው የድለላ ድርጅቶች አማካይነት ለግርድና ወደአረብ አገር የሚጎርፉት፤ የፈላ ዜይት ገላቸው ላይ እየተደፋና ከፎቅ እየተወረወሩ በመገደል ላይ ያሉ ሴት እህቶቻችን ገና በወጣትነት ዕድሜ ያሉ ናቸው። በህገ ወጥ መንገድ ባህር አቋርጠው በጀልባ ሲጓጓዙ ባህር ውስጥ ሰጥመው የአዞ እራት የሆኑት አብዛኛው ወጣቶች ናቸው። አገርን የመሰለ የለምና ምንም ቢከፋን የትም አንሄድም ያሉት ደግሞ የልዩ ልዩ አደንዛዥ እጽ ሱሰኞች እንዲሆኑ ፤ ለኤድስ ወረርሽኝ እንዲጋለጡና ተስፋ እንዲቆርጡ የሚደረጉት ወጣቶች ናቸው። የወጣቶችን ሞራል በዚህ አይነት መልኩ ማላሸቅ መለስ ዜናዊ ከጥንት ጀምሮ ሲያስብበት የኖረው የሶሻል ኢንጂነሪንግ እኩይ ሃሳቡ አንዱ ክፍል ነው።

የነመለስ ዜናዊ ሌላው ሲሻል ኢንጂነሪንግ ሌላው አካል የሚጠሉትን ብሄረሰብ ቁጥር በረቀቀ ዜዴ እንዲቀንስ ማድረግ ነው። በቅርቡ ተደርጎ በነበረው የህዝብ ቆጠራ የአማራው ህዝብ ቁጥር በሁለት ሚሊዮን ቀንሶ እንዲመዘገብ መደረጉ አይነተኛ ማስረጃ ነው። ስለ አማራ ህዝብ ቁጥር መቀነስ የተጠየቀው መለስ ዜናዊ በሰጠው ምላሽ "የአማራ ህዝብ በኤድስ ምክንያት ቁጥሩ ቀንሷል" የሚል ነበር። ይህ አባባል ምን ያህል ንቀት የተሞላበት እንደሆነ የሚያከራክር አየደለም።

መለስ ዜናዊ ህግ በሆነበት አገር እርሱ ይሁን ያለው ሁሉ ሲሆን ማየት የተለመደ ከሆነ ሰነባብቶአል።አይሆንም ካለም አይሆንም። ዜጎች የሚገባቸውን ነጻነት እስከ ምን ደረጃ እንደሆነ የመመደብ ሃይል የተላበሰው መለስ ወጣቱ ለነጻነቱ የሚያነሳቸውን የዜግነት መብቶች አረንጓዴና ቀይ በሚል መስመር ውስጥ ከልሎአቸዋል። አረንጓደው መስመር የርሱን አልሻዳይነት ተቀብሎ ጸጥ ለጥ ብሎ መገዛት ሲሆን ቀዩ መስመር የተባለው የርሱን የስልጣን አልሻዳይነት አልመቀበል ነው። ይህ ደግሞ በሽብርተኝነት ወንጀል ያስጠይቃል መለስ ዜናዊ ህግ በሆነበት አገራችን።

አገራችን በእንዲህ አይነት ጨካኝና ኃላፊነት በማይሰማቸው ሃይሎች እጅ በመውደቋ የተነሳ የቻለው ሁሉ ስደትን እንደ አማራጭ ተያይዞታል። ወጣቱን ትውልድ ለስደት እያመቻቸ ያለው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ሽማግሌዎችን ያለጧሪ የሚያስቀር፤ እናቶችን የወላድ መካን የሚያደርግ፤ ልጆችን ያለወላጅ የሚያስቀር ሆኖአል።ለዚህም ነው የእፍኝት ልጆች የሚባሉት።

እፍኝት ክፍ እንስሳ ነች።ስትረገዝ አባቷን ትገድላለች።ስትወለድም እናቷን ገድላ ትወለዳለች።ከዚያም ያለወላጅ ታድጋለች።እነመለስ ዜናዊም እንዲህ ናቸው። አባቶቻችን በደማቸው ክፍያ ያቆዩልንን አገር ለባዕዳን በመሸጥ ፤ ያወረሱንን የነጻነት መንፈስ በመገደል፤ ለስደትና ለስቃይ ዳርገውናል። ከአያት ቅድሜ አያት የወረስናቸው እሴቶችና መልካም ስነምግባሮች ሆን ብለው እንዲጠፉ እየተደረገ ነው።

የመለስ አገዛዝ ዜጎችን አዶንቅሮ ለመግዛት ካለው ፍላጎት የተነሳ በመላው አለም የተዳረሰው የኢንፎርሜሽን ቴኪኒኦሎጂ በአገራችን እንዳይኖር ተደርጎአል።ትናንት ነጻነቷን የተቀዳጀቺው ኬኔያ በብዙ ፈርጁ ከኢትዮጵያችን ትሻላለች።አንድ የኬኒያ ወጣት በራሱ ቋንቋ ከሚነገሩ አስራ አንድ የግል የቴሌቭዥን ጣቢዎች መካከል የፈለገውን መርጦ ማየት ሲችል የኢትዮጵያ ወጣት ግን ለዚህ የታደለ አይደለም።አንድ የኬኒያ ወጣት ኢንቴርኔት ከፍቶ የኢሜይል መልእክቱን ለማየት አንድ ደቂቃ ብቻ ሲበቃው የኢትዮጵያው ወጣት ግን ተመሳሳይ መልእክት ለማየት ስድስት ደቂቃ ይፈጅበታል።

ለምን እንዲህ ይሆናል ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ ግልጽና አጭር ነው።የመለስ ዜናዊ ስሜት ስላልፈቀደ ነው።

መለስ ዜናዊ በተፍጥሮው “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” እንዳለችው ዓይነት እንስሳ ስለሆነ የኢትዮጵያ ወጣቶች በነገ አገራቸው ጉዳይ ላይ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አይፈልግም።ሆን ብሎም በአገሪቷ ውስጥ የሺሻና የጫት ኪዮስኮች ያለገደብ እንዲባዙ አድርጎ ወጣቶች በአልባሌ ነግሮች ወርቃማ ግዜያችውን ሲያጠፍ መለስ በዚህ እፎይ ይላል።መለስ ዜናዊና ልጆቹ በዓለም ላይ የሚሆነውን የሚከታተሉበት የተለየ የኢንቴርኔት አገልግሎትና የተለየ የሳታላይት መሥመር አሏቸው።የኢትዮጵያ ወጣቶች መለስ ዜናዊ መጥኖ ከሚሰጣቸው እጅ እጅ ከሚል ፕሮፖጋንዳ በስተቀር በገዛ አገራቸው የሚፈጸመውን መረጃ እንዳያገኙ ታግደዋል።

የቱኒዚያው ቤኒ ዓሊና የግብጹ ሆስኒ ሙባረክ የመለስን ያክል ለወጣቶቻቸው ጨካኞች አልነበሩም።የእነዚህ አገራት ወጣቶች በዓለም ዙሪያ ካሉ ከእድሜ አቻዎቻቸው ጋር በፌስ ቡክ፤በቲውተርና በኢሜይል እየተገናኙ ስለነጻነት፤ስለፍትህ፤ስለ ሰብዓዊ መብት፤ስለየህግ የበላይነት ምንነት ይወያዩ ነበር ።ቤኒ ዓሊና ሆስኒ ሙባረክ ወጣቶቻቸው ዘመኑ ከፈጠረላቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ጋር እንዲተዋወቁና እንዲጠቀሙበት አድርገዋል።መለስ ዜናዊ ግን ከእነዚህ የከፋ ጨካኝና ለአገሩ ወጣቶች ቅንጣት ታክል ፍቅርና ክብር የሌለው በመሆኑ ከመጀመሪያው ጀምሮ ዜጎች ዘመኑ ከፈጠረላቸው ቴክኖሎጂ ጋር እንዳይተዋወቁ አድርጓል።

ይሄ ሊቆጨን ይገባል።

ዓለም እንዲህ እደዛሬው ባልሠለጠነበት የድንጋይ ዘመን ከሥልጣኔ ማማ ላይ የነበረቺው አገራችን ኢትዮጵያ፤ መላው የአፍሪካ ፤ የኤሺያ የመካከለኛው ምሥራቅ አገራት በባርነት ቀንበር ሥር ይሰቃዩ በነበሩበት የቅኝ ግዛት ዘመን የራሷን ሉዓላዊነት ከማስከበር አልፋ ለሌሎች ነጻነት በአለም አደባባይ ብቻዋን ትፋለም የነበረቺው አገር ኢትዮጵያ፤ ዛሬ ከአብራኳ ክፋይ በተገኙ ባንዳዎች ተዋርዳና ተከፋፍላ የረሃብ፤ የድንቁርናና የኋላቀርነት ተምሳሌት ሆናለች። በዚህም የተነሳ የኢትዮጵያ ወጣቶች ነጻ ከወጡ ገና ግማሽ ምዕተ ዓመት ብቻ ከሆናቸው የቱኒዚያ፤የኬኒያ፤የግብጽ እና የጋና ከመሳሰሉት አገሮች ወጣቶች ሳይቀር አንሰው ይገኛሉ። የኢትዮጵያ ወጣቶች ለንጽፅር ከጠቀስናቸው አገሮች ተለይተው ዘመኑ ከደረሰበት ቴክኖሎጂ ጋር እንዳይተዋወቁ የሚያደርጋቸው የመለስ ዜናዊ ስሜት ብቻ ነው።የመለስ ዜናዊ ስሜት ህግ በሆነበት በዚህ ግዜ ለነጻነቱ ቀናዒ የሆነ ወጣት መነሳት አለበት።

የቱኒዚያው ወጣት ሙሃመድ ቡዛዚ 26 ዓመቱ ነው።በዚህ እድሜው ዩንቨርስቲ ገብቶ በኮምፒውተር ሳይንስ ቢመረቅም የቤኒ ዓሊ ዘመድ ወይም ደግሞ የእርሱ የመንደር ልጅ ስላልሆነ በሙያው ሥራ ሊቀጠር አልቻለም።ጦም ከማደር ብሎ ፍራፍሬ እያዞረ ሸጦ ኑሮውን ለመግፋት ወሰነ።በቤኒ ዓሊ ዘመዶችና ባለሟሎች የተያዘው ቢሮክራሲ ሙሃመድ ቡዛዚ ብቸኛ የገቢ ምንጩ የሆነውን የንግድ መሣሪያውንና ፍራፍሬውን ፈቃድ የለህም ብለው ወረሱበት።አቤት የሚልበትን አጣ።ሁሉም በዘመድ ሁሉም በቤን ዓሊ የሚወሰን ሆነበት።እንዲውም ህግን ያስከብራሉ ተብለው የተሰየሙ ከህግ በላይ ሆነው መሃመድ ፈቃድ እንዲሰጡት ቢጠይቃቸው በጥፊ መቱት።ተዘባበቱበት።

ከዚያም ሙሃመድ ራሱን በእሳት አጋይቶ በቱኒዚያ የመጣውን ለውጥ አቀጣጠለው።ዛሬ ሙሃመድ የነጻነት ምሳሌ ሁኖ በመላው ዓለም ስሙ የታወቀ ሁኗል።ታሪክም ይሄን እያስታወሰ ይኖራል።

ያለነጻነት መኖር ውርደት ነው።ኢትዮጵያዊያን ወጣቶች ተዋርዶ መኖርን ከአያቶቻቸው አልተማሩም።አያቶቻቸው በተለያዩ ጊዜያቶች ነጻነታቸውን ለመገርሰስ የቃጡትን ጠላቶች በየተራ ድባቅ መተው በመመለስ የዛሬው ትውልድ የሚኮራበትን ታሪክና የነጻነት ቀንዲል ትተው አልፈዋል።

በመለስ ዜናዊ ዘረኛ የአምባገነን ሥርዓት ነጻነታቸውን የተቀሙት የዛሬው የአገሪቷ ወጣቶች ዘመኑ የፈጠረላቸውን ቴክኖሎጂ እንኳ በአግባቡ እንዳይጠቀሙ ተገድበዋል። ይህን አፈና አሻፈረኝ ማለትና የተነጠቀውን ነጻነት ማስመለስ የወጣቶች መብት ግዴታ ነው።ኢትዮጵያ መለስ ዜናዊን የመሰሉ የእፍኝት ልጆች ሳትሆን የብዙሃን ወጣቶች አገር ነች።ወጣቶች ያለምንም ገደብ የፈለጉትን መገናኛ መንገድ ተጠቅመው በዓለማችን ላይ ምን እየተደረገ እንደሆነ ሲያውቁ የአገራቸውንም ጉዳይ በተመለከተ ከተለያየ ምንጭ መረጃ አግኝተው ይበጃል ያሉትን ሲደግፉ ያን ግዜ ለብሩህ ህይወታቸው የሚበጃቸውን ለመወሰን ዕድል ያገኛሉ።

ዛሬ የኢትዮጵያ ወጣቶች በነጻነት ኑረው በነጻነት ማሰብ እንዳይችሉ መለስ ዜናዊ እንቅፋት ሁኗል።ስለሆነም ወጣቱ ነገ የተዋበችና ሁሉም ዜጋ በነጻነት የሚኖርባት አገር እንድትኖረው መለስ ዜናዊንና ዘረኛ ቡድኑን ግንባሩን ሳያጥፍ መታገል ይጠበቅበታል።ወጣቱ ለሚያድርገው ማንኛውም ትግል ግንቦት ሰባት የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ከጎኑ ይቆማል። አስፈላጊውንም እገዛ ያደርጋል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!!**

### የኤፈርት ኩባንያ አካል የሆነው ሳባ ኢንጂነሪንግ የአስራ አንድ ነጥብ አራት ሚሊዮን ብር . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዉስጥ እንዲከፍል ሁኔታዎች የተመቻቹለት ቢሆንም እስከዛሬ ድረስ ምንም ሳይከፍል መቆየቱን ከዘገባው ለመረዳት ተችሏል። “ጌታዋን የተማመነች በግ ላቷን ውጭ ታሳድራለች” እንደሚባለው ህወሃቶች በርካሽ ዋጋ ወደስማቸው ያዛወሩትን የመንግሥትና የህዝብ ንብረት ላለፉት 4 አመታት ያህል ሰርተውበት ከግዢው ዋጋ በላይ ትርፍ ያጋበሱበት ቢሆንም በዕዳነት ያለባቸውን የህዝብ ገንዘብ ለመክፈል ፍቃደኛ ያለመሆናቸውን ይህ ለህዝብ ይፋ የሆነው ዘገባ አጋልጧል።

የሳባ ኢንጂነሪንግን ሽያጭና ግዢ በሚመለከት ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውና ስማቸው እንዳይገለጽ የጠየቁ አንድ የኩባንያው ሰራተኛ በሰጡት አስተያየት ሻጭና ገዢ የሆነው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ህዝብ ንብረት ብቻ ሳይሆን በህዝቦቿና በአገሪቱ ሉአላዊነት ላይ የፈለገውን ደባ ሲፈጽም የነበረ ስለሆነ ከ20 አመት አገዛዝ በኋላ ሥልጣናቸው የሚገረሰስ ስለማይመስላቸው ይፈንጩ ብለው ነው እንዲህ አይነት ዜና ወጣ እንጂ ኢፌርት የሚቆጣጠራቸው ድርጅቶች ሁሉ በተመሳሳይ መንገድ መገኘታቸውን ህዝብ መቼ ያጣዋል ብለዋል።

ኤፈርት በአሁኑ ሰዓት የአገሪቱን አብላጫ የንግድ እንቅስቃሴ የሚቆጣጠር ባለ ብዙ ቢሊዮን ዶላር ባለሃብት ኩባንያ ሲሆን የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን በዋና ሥራ አስኪያጅነት የምትመራው ድርጅት እንደሆነ ይታወቃል።

## ነጻ ሚዲያን ከጦር በላይ የሚፈራው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ አገዛዙን የሚቃወሙ ድምጾችን ማስራጨት እንዲያቆም ለአሜሪካን መንግሥት አቤቱታ አቀረበ

ልማትና ዲሞክረሲን ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አስተዋዉቅያለሁ ደግሞም ባለፉት 7 አመታት በተከታታይ ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግቢያለሁ ስለዚህም ህዝብ ይወደናል እንደዚህማ ባይሆን ኖሮ 99% የምርጫ ድምጽ አግኝተን አንመረጥም ነበር እያለ እራሱንም ሆነ የአለምን ህዝብ የሚያታልልዉ የዘረኛዉ መለስ ዜናዊ አገዛዝ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የተቃዋሚዎችን ሃሳብ እንዳይዘግብ አደርጉልኝ ሲል መማጸኑን የቪኦኤን የአማሪኛ ዝግጅት ክፍል ባለፈው ሃሙስ መዘገቡ ተሰማ፡፡ የመለስ አገዛዝ አቤቱታውን ያሰማው የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮን ለሚያስተዳድረው ቦርድ ሰሆን የቦርዱ አባላት በቅርቡ ኢትዮጵያ ዉስጥ የስራ ጉብኝት ባደርጉበት ወቅት በአገዛዙ ስም አቤቱታዉን ያቀረቡት የኮሚኒኬሽንስ ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር የሆነዉ በረከት ስምዖንና ሌሎችም ከፍተኛ የአገዛዙ ባለስልጣናት እንደሆኑ የቪኦኤ ዘገባ ያመለክታል፡፡

እንደ ቪኦኤ ዘገባ፤ የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮን የሚያስተዳድረው ቦርድ የአፍሪካ ቀንድ አገልግሎት ወደ ኢትዮጵያ የተጓዘው በፕሬዝደንት ኦባማ ተወክሎ ሲሆን የጉዞዉ አላማም ከወያኔ አገዛዝ ጋር ያለውን ግንኙነትና ትብብር ለማጠናከር፣ በመገናኛ ብዙኋን አቅም ግንባታ ላይ ለመሳተፍና፣ ተጨማሪ ዜና ለመሰብሰብ የሚያስችለውን አቅም ለመገንባት በማሰብ ነበር፡፡

ኢትዮጵያን የጎበኘው የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ የአስተዳደር ቦርድ ልዑካን ቡድን በቡሽ አስተዳድር ወቅት የዋይት ሃውስ ቃል አቀባይ የነበሩት ዳና ፔሪኖ ፤ ሚስ ሱዛን መኩ እና ሚስተር ማይክል ሚሃን እንዲሁም ሌሎች የቪኦኤ ሰራተኞች ያሉበት ቡድን እንደሆነ ታውቆአል፡፡

የልኡካን ቡድኑ ተልዕኮ ዋና አላማ የኢትዮጵያው አገዛዝ ከአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ ጋር የገባውን የሻከረ ግንኙነት እንዲያሻሽልና በተለይ አለም አቀፍም ሆነ አህጉራዊ ህጎችን በሚጻረር መልኩ የአማርኛ፣ ትግርኛና ኦሮሚኛ ቋንቋ ስርጭቶችን ማፈኑን እንዲያቆም፤ በምትኩ ለተሻለ አገልግሎት በሁሉም ክልሎች ዜና ለማሰባሰብ የሚያስችለውን መረብ ለመዘርጋት እንዲያስችለው ለማነጋገር እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

የአሜሪካ ድምጽ ጋዜጠኞችን ከተቃዋሚዎች ጎራ ከመፈረጅ አልፎ በድህረ ምርጫ 97 በዘር ማጥፋት ወንጀል ከተከሰሱት የቅንጅት መሪዎች ፋይል ጋር ስማቸው ፍርድ ቤት እንዲቀርብ አድርጎ የነበረው የመለስ በረከት አገዛዝ በበኩሉ ፤ አሁንም የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ዘገባ ሚዛናዊ አየደለም ፤ ለተቃዋሚዎች ያደላና፤ የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባር የጎደለው ነው በማለት እንደሚከስ እና ከሳምንታት በፊት 41 ገጽ የያዘ የክስ ዝርዝር አዲስ አበባ ለሚገኘው የዩናይትድ ስቴይትስ ኢምባሲ ማስገባቱን የቪ ኦ ኤ ዘገባ ገልጿል፡፡

ከበረከት ስሞዖን ጋር ውይየት ያደረገው የልኡካን ቡድን አባል የሆኑት የአፍሪካ ክፍል ሃላፊው ዴቪድ አርኖልድ ለቪ ኦ ኤ ጋዜጠኛ እንደገለጹት ፤ የወያኔዎች ክስ “የአሜሪካ ድምጽ ሬድዮ በዝግጅቶቹ የሚያቀርባቸው እንግዶች ለኢትዮጵያ መንግስት በጎ አመለካከት የላቸውም፤ አንዳንዶቹ ጽንፍ የረገጡ ተቃዋሚዎች ናቸው” ስለዚህ በአጭሩ “አሁንና ቀድሞ በፖለቲካ የተሳተፉና ከኢትዮጵያ መንግስት የተለየ ሃሳብ ያላቸውን ሰዎች ሃሳብና ራእይ ለኢትዮጵያ ህዝብ አታቅርቡ “ የሚል እንደሆነና ይህ ደግሞ ሚዛናዊ መረጃን ለህዝብ ማቅረብ ዋና አላማው ላደረገ እንደ የአሜሪካ ድምጽ አይነቶቹ የሚዲያ ተቋማት የሚታለምም የሚቻልም አለመሆኑን ተናግረዋል፡፡

የመለስ በረከት አገዛዝ በአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ፍጹም እንዳይቀርቡ የሚፈልጋቸውን ሰዎች ሥም ዝርዝር ለአሜሪካ መንግሥት ያቀረበ ሲሆን ከነርሱም ጥቂቶቹ ዶር ጳውሎስ ሚልኪያስ፤ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ፤ ዶር ጌታቸው መታፈሪያ ፤የኤርትራው ማስታወቂያ ምንስትር አቶ አሊ አብዶ፤ ዶር መራራ ጉዲና፤ ዶር ብርሃኑ ነጋ፤ አቶ ግርማ ሞገስ ፤ አቶ ስዬ አብረሃ ወዘተ መሆናቸውን ዴቪድ አርኖልድ መናገራቸውን የአማርኛው ዝግጅት ክፍል ገልጿል፡፡

## ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ጋዜጠኞችን ማሳደዱን ቀጠለ፣ የአውራ አምባ ታይምስ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ለአንድ ቀን በማ እከላዊ እስር ቤት ታስሮ ተፈታ፣ የጋዜጣ ታዳሚ ወጣት ርእዮት ዓለሙ በሽብተኝነት ወንጀል ታሰረች

በቱኒዚያ ህዝባዊ አብዮት ፈንድቶ የሰሜን አፍሪቃ ሃገራትን ካዳረሰና በመላው አፍሪቃ የሚገኙ የአምባገነን አገዛዞችን በር ማንኮታኮት ከጀመረ ወዲህ በእንቅልፍ እጦት የሚባንንነዉ አምባገነኑ መለስ ዜናዊና ዘረኛ ስርዐቱ የአውራ አምባ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ የሆነዉን ወጣት ዉብሸት ታዬን እስር ቤት መወርወሩ ታወቀ፤ይህ የጋዜጠኞች ጠላት የሆነዉ ስርዐት የዉብሸት መታሠር ዜና እንደተሰማ ብዙም ሳይቀይ ባለፈው ማክሰኞ ደግሞ የጋዜጣውን ዋና አዘጋጅ ዳዊት ከበደን ለአንድ ቀን አስሮ መልቀቁ ተገለጸ፡፡ በተመሳሳይ ዜና የዘረኛውን ወያኔ አገዛዝ ኢፍትሃዊ የሆነ አስተዳደር በተባዉ ብዕሯ በማጋለጥ የምትታወቀው ወጣቷ የሰብአዊ መብት ተሟጋችና የቋንቋ መምህርት የሆነቸዉን ወይዘሪት ርእዮት አለሙ ባለፈው ማክሰኞ በፌደራል ፖሊስ ቁጥጥር ስር መዋሏ ታውቋል፡፡

የወጣት ርእዮት ቤተሰቦች እንደገለጹት የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ፌደራል ፖሊስ ወጣቷን በቁጥጥር ስር እንድትውል ያደረገው እንግሊዝኛ ቋንቋ ከምታስተምርበት ቀጨኔ ደብረሰላም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዉስጥ በማስተማር ስራዋ ላይ እንዳለች መሆኑ ታውቋል፡፡ እንደ ዜና ምንጮቻችን ዘገባ ወጣት ርዕዮት ለእስር የተዳረገችበት ምክንያት ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ ህገመንግስታዊ መብቷን ተጠቅማ በሃገር ውስጥ በሚታተመው የፍትህ ጋዜጣ ላይ በአምደኝነት በመሳተፍ በዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ላይ በምታቀርባቸው በሳል ፖለቲካዊ ትችቶች የተነሳ እንደሆነ ታውቋል፡፡

ወይዘሪት ርእዮትን በቁጥጥር ሥር ያዋለው የፌደራል ፖልስ ሽሮ ሜዳ አካባቢ ወደሚገኘው የቤተሰቦቿ መኖሪያ ቤት ከወሰዷት በኋላ ፣ ክፍሏን እስከ ቀኑ አስር ሰአት ድረስ የፈተሹና የበረበሩ ሲሆን በቤቱዋ ውስጥ ምንም ነገር ሲያጡ ወደ ፌደራል ማእከላዊ ፖሊስ ምርመራ ቢሮ በመውሰድ እንዳሰሯት የደረሰን መረጃ ያመለክታል፡፡

ወጣት ርእዮት የኢትዮጵያ ፌደራላዊት ዲሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ ጽ/ቤት ሃላፊ የሆኑት የአቶ ዓለሙ ኩየራ ልጅ ስትሆን የአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ንቁ አባል የነበረችና ቀደም ሲልም በህትመት ላይ በነበረው አዲስ ፕሬስ ጋዜጣ ላይ በአዘጋጂነት ታገለግል እንደነበር የመረጃ ምንጮቻችን አክለው ገልጸዋል፡፡

ወይዘሪት ርእዮት ዓለሙ ባለፈው ረቡእ ሰኔ 15 ቀን 2003 ዓም ከቀኑ ስምንት ሰአት ላይ አራዳ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዝግ ችሎት ቀርባ የተወነጀለችው በአሸባሪነት ክስ መሆኑ እንደተነገራት ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፍትህ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ተመስገን ደሳለኝ ሰሞኑን በሙያው የተነሳ የተለያዩ የእጅ አዙር ጫናዎች እየደረሱበት እንደሆነና በዚህም ሳቢያ የዝግጅት ክፍሉ ስጋት ላይ መውደቁን ከኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ጋር ባደረገው ቃለ ምልልስ ገልጿል፡፡ ጋዜጠኛ ተመስገን አምደኞቹ ከታሰሩበትና የደረሱበት ከጠፋ ጊዜ ጀምሮ ለደህንነት ቢሮ ቅርበት አለን የሚሉ ሰዎች በተንቀሳቃሽ ስልኩ በተደጋጋሚ እየደወሉ ስራውን የማያቆም ከሆነ እሱንም በ አሸባሪነት በመወንጀል ወደ እስር ቤት እንደሚወረውሩት እየፎከሩበት መሆኑን በቃለ ምልልሱ ላይ አስታውቋል፡፡

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ህዝብን በጠመንጃ አፈሙዝም አፍኜና ረግጬ መግዛት እችላለሁ ከሚለው ከንቱና ደካማ ቅዠት በመነሳት በንጹሃንና ለሃገር ተቆርቋሪ በሆኑ ዜጎች ላይ የተለያዩ የወንጀል ታርጋ በመለጠፍ ሲያስር፣ ሲያሰቃይና ሲገድል እንደቆየ በስፋት ይታወቃል፡፡

## የኦጋዴን ነጻ አውጪ ድርጅት የ አመራር አባል በስደት ይኖሩበት በነበረው ኬንያ መገደላቸው ታወቀ

የኦጋዴን ነፃነት ግምባር የውጭ ግንኙነት ክፍል አባልና የኢትዮጵያ ጉዳዮች ዘርፍ ተወካይ የሆኑት አቶ ሃሰን አብዱላሂ ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደተናገሩት የኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት የማእከላዊ ኮሚቴ አባል የነበሩት አቶ አብዱላሂ ሰኢድ በወያኔ የጸጥታ ሃይሎች ናይሮቢ ኬንያ ውስጥ መገደላቸውን ማረጋገጣቸውን ኢሳት ዘገበ፡፡

እንደ ኢሳት ዘገባ ግለሰቡ በጁን 21 ቀን ላይ ታፍነው ከተወሰዱ በኋላ በጥይት ተደብድበው ተገድለዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ የኦጋዴን ነጻ አውጪ ድርጅት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በጦርነት ሜዳ ላይ ሽንፈት ሲደርስበት እንዲህ አይነት አረመኔያዊ ርምጃ መውሰዱን አቶ ሃሰን መግለጻቸው ታውቋል፡፡

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ከአሁን በፊት የኦጋዴን አመራር አካላትን ለመግደል ሞክሮ እንዳልተሳካለት የገለጹት አቶ ሃሰን በቅርብ ጊዜ ውስጥ የ አቶ አብዱላሂ ሰኢድን ሞት እንደሚበቀሉ በቁርጠኝነት መግለጻቸውን ኢሳት ዘግቧል፡፡

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ ቦታዎችና ጊዜያቶች ለጆሮ እጅግ የሚሰቀጥጡ ወንጀሎችን በተደጋጋሚ ሲፈጽም እንደቆየ በስፋት ሲዘገብ የቆየ መሆኑ ይታወቃል፡፡

## ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም አይ ኤም ኤፍ በኢትዮጵያ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ቢያንስ ሶስት ነጥብ አምስት ሚልዮን የሚገመት ህዝብ የአስቸኳይ ጊዜ የምግብ ርዳታ ጥገኛ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ በያዝነው ዓመት የዋጋ ግሽበቱ 35 በመቶ መድረሱ በስፋት መዘገቡ ይታወቃል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ የታየውን ያክል ባይሆንም በተለያዩ የአፍሪቃ ሃገራት የዋጋ ግሽበት የተከሰተ ሲሆን በተለይም ኡጋንዳ ዉስጥ ከኑሮ ውድነት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የሆነ ህዝባዊ አመጽ መቀስቀሱ ይታወሳል፡፡

ኢትዮጵያዊያን የዋጋ ንረቱንም ሆነ የዘረኛው አገዛዝ አስተዳደራዊ ችግሮች በተለያየ መንገድ እየታገሉ ሲሆን ይህ የየአካባቢዉ ትግል ወደ ህዝባዊ አመጽ እንዳይቀየርና ወያኔን ጠራርጎ የሚሄድ አብዮት እንዳይቀሰቅስ የወያኔ ቁንጮዋች በየቦታዉ የቀቢፀ ተስፋ እርምጃ በመዉሰድ ላይ መሆናቸዉን ለማወቅ ተችሏል፡፡ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ " አገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎችን አስተያየት ለኢትዮጵያዊያን አድማጮቹ እንዳያቀርብ እገዳ ይደረግበት" ሲል 41 ገጽ አቤቱታ ለአሜሪካ መንግሥት ማቅረቡ ከተስፋ መቁረጥ ምልክቶች አንዱ ማስረጃ እንደሆነ የደረሱን የህዝብ አስተያየቶች አመልክተዋል፡፡

ዓለም አቀፉ የገንዘብ ተቋም “አይ ኤም ኤፍ” የወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ በቅርቡ በፍጆታ ዕቃዎች ላይ ጥሎት የነበረውን የዋጋ ተመን ማንሳቱ ተገቢ እርምጃ ነው ካለ በኋላ አገዛዙ አሁንም በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ እየታየ ያለውን ቀውስ የማስተካከያ ርምጃ በስፋት መውሰድ እንዳለበት አስገንዝቧል፡፡

የወያኔው ኢሃዴግ የንግድ ሚንስቴር ሹመኛ በ ቪ ኦ ኤ ቀርቦ ባደረገው ቃለ ምልልስ የሸቀጦች የዋጋ ተመን የወጣው በቂ የሆነ ጥናትና ዝግጅት አድርገንበት ነው፤ ከአጭር ጊዜ ትግበራ በኋላም የዋጋ ተመኑን ስናነሳ እንደዚሁ በቂ ጥናትና ዝግጅት አድርገን ነው በማለት አስቂኝ የሆነ ምላሽ መስጠቱ ይታወሳል፡፡


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው፡፡**

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን፡፡


**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን፡፡ g7radio@ginbot7.org